## ቸ/ የመጽሐፍ ቅዱስና የሳይንስ አንድነትና ልዩነት ማወቅ

ከዚህ በተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስና የሳይንስ አንድነ ትና ልዩነት መረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን እውነቶች በተገቢው ሁኔታ እንድንረዳ ይጠቅመናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ከሳይንስ ጋር የማይጋጭበትም አጋጣሚ አለ፤ የሚጋጭበትም ሁኔታ አለ::

ሳይንስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈሳዊና ቁሳዊ እውነቶች ጋር ሊስማማም ላይስማማም ይችላል:: ሳይንስ መንፈሳዊ የሆነውን እውነት በቤተሙከራ አስገብቶ እውነት ወይንም ሐሰት እንደሆነ ማረጋገጥ ስለሚቸግረው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ጋር ላይስማማ ይችላል:: በሌላ አንጻር ደግሞ ሳይንስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ቁሳዊ እውነቶችን ስለ እውነተኛነታቸው ድጋፍ ይሰጣል:: ሆኖም ግን ሳይንስ በራሱ ውስንነት የለውም ማለት አይደለም:: ስለዚህ ሳይንስ የሚለውን ሁሉ እውነት እንደሆነ አምነን መጽሐፍ ቅዱስን ለመኮነን ከተነሳን እንሳሳታለን:: የሳይንስን ውስንነት ከምናይባቸው መንገዶች አንዱ በአንድ ዘመን የነበረው ሳይንቲስት ፍጹም እውነት ነው ብሎ ያስተማረውን ትምሕርት ሳይንሳዊ ቲዎሪ ሌላው ሳይንቲስት መጥቶ ሲያፈርሰው እንመለከታለን::

ሳይንስና ሳይንቲስቶችም የመጡት እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ ነው፤ ጥናታቸውም የሚያደርጉት ፈጣሪ ቀድሞ በሰ ራው ነገር ነው::መጽሐፍ ቅዱስ ግን እግዚአብሔር ቀድሞ ስለሠራ ውና ስለ ሰው ጭምር የጠለቀ መግለጫ ይሰጣል:: መጽሐፍ ቅዱስና ሳይንስ ስለ አንድ ነገር የሚሰጡት ገለጻም በተለያየ መንገድ ነው;; መጽሐፍ ቅዱስ ምን ተፈጸመ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል:: ይህም ማለት ብዙም ጊዜ አንድን ነገር ወደዚያ ደረጃ መምጣቱን እንጂ እንዴት እንደመጣ ዝርዝሩን አይነግረንም:: ነገር ግን ሳይንስ አንድን ነገር እንዴት እንደመጣ

/እንደተከሰተ/ ዝርዝር ማብራሪያ ይሰጣል። ይህ የሚያሳየው የመጽሐፍ ቅዱስና የሳይንስ ትኩረት የተለያየ እንደሆነ ነው። የተለያየ ሕግና ሥርዓት ያላቸውን ነገሮች ሆነው ሳሉ ሳይንስን ብቻ በመጠቀም ልዩነቶችን ሳያገናዝቡ መጽሐፍ ቅዱሱን መኮነን አግባብ አይደለም። በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ተአምራት ከሳይንስና ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ በልዑል እግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት የሚፈጸሙ ስለሆኑ በሳይንስ መመዘኛ መጽሐፍ ቅዱስን መመዘን አይገባንም። ይህ እንዳለ ሆኖ ሳይንቲስቶች ስለ አለፉት ነገሮችና ወደፊት ስለሚሆኑት ክስተቶች መላምቶችን /(Assumptions or theories) ይሰጣሉ። እነዚህ መላምቶች አንዳንዴ እውነትነት ሲኖራቸው በሌላ ጊዜ ደግሞ እውነት ሳይሆኑ ይቀራሉ። ለምሳሌ ስለሰማይና ምድር አፈጣጠር ሳይንቲስቶች መላ ምቶችን ሰጥተዋል። ነገር ግን ትክክለኛ መረጃ የምናገኘው በመላ ምት ሳይሆን ፈጣሪ አምላክ ፍጥረቱን እንዴት እንደፈጠረ ከሰጠው መገለጥ ነው።በዚህ አጋጣሚ ማሳሰብ የምፈልገው ሳይንስ ውስን ስለሆነ ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ መደገፍ ባንችልም ሳይንስን አንቃወምም።

ከዚህ በተጓዳኝ ጸሐፊዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሲጽፉ በእለት ተዕለት መግባቢያ ቋንቋ (common Language) እንጂ የዘመኑ ቴክኒካል የሳይንስ ቋንቋዎች ተጠቅመው አይደለም። ስለዚህ ስንተረጉም የጸሐፊዎች የቋንቋ አጠቃቀምና የአገላለጽ ስልት ልንከተል ግድ ነው።ለምሳሌ በኢያ.10:12-14 ፀሐይ በገባኦን ላይ እንደቆመች ሲያመለክት እንዲህ ብሏል፤ «በሰማይ መካከል ዘገየ፣ አንድ ቀንም ሙሉ ለመግባት አልቸኮለም።» ሲል በመክ.1:5 ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን። የኢያሱ እና የመክብብ መጽሐፍ ጸሐፊዎች ጸሐይ በምሕዋር ውስጥ ትዞራለች ማለታቸው አይደለም አሁንም ቢሆን በመደበኛ አነጋገር ጸሐይ ከምሥራቅ ወጥታ ወደ ምዕራብ ትጠልቃለች እንላለን። ሳይቲስቶችም እንኳ በመግባቢያነት የሚጠቀሙት እንዲሁ ነው።ቴክኒካል በሆነ የሳይንስ ቋንቋ ተጠቅመው ለመናገር ከፈለጉ እንጂ የነጋው ወይንም የመሸው መሬት በራስዋ ዛቢያ

ስለምትዞር ነው አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስም ሲጻፍ እግዚአብሔር ሳይንሳዊ የሆኑትን ነገሮችን ስለማያውቅ ሳይሆን ሰዎች በቀላሉ መረዳት የሚችሉት በእለት ተዕለት መግባቢያ ቋንቋ ሲገለጽላቸው ስለሆነ ነው:: ሌላው በተደጋጋሚ የሚነሳው ሐሳብ በዘፍ.1:3 «እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ» ካለ በኋላ ብርሃንን የሚሰጡት አካላት /ፀሐይ፣ጨረቃና ከዋክብት/የተፈጠሩት በዘፍ.1፡14-18 ወይንም በአራተኛው ቀን ነው::እነዚህ ብርሃን ሰጪ አካላት ሳይኖሩ ብርሃን ከየት መጣ? የሚል ጥያቄ ይነሳል:: አንዳንዶች ይህ አገላለጽ ከሳይንስ ሕግ ውጪ ነው ይላሉ::የጥያቄው መነሳት አስፈላጊነት ግልጽ ቢሆንም የብርሃን ምንጮች ፀሐይ ፣ጨረቃና ከዋክብት ብቻ እንዳልሆኑ ማስተዋል ይኖርብናል:: በዘፍ.1:3 «ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ» ሲል የብርሃኑ ምንጭ አይጠቀስም::ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ይሁን ያለው ነገር ሁሉ ስለሚሆን ብርሃኑ ከየትም ይምጣ ከየት ብርሃን ሆኖአል:: እነዚህ ብርሃን ሰጪ አካላት ስላልተፈጠሩ ብርሃን እንዴት ይኖራል ብሎ መጠየቅ የዋህነት ነው:: በዘመናችንም እንኳን የብርሃን ምንጮች እነዚህ አካላት ብቻ አይደሉም:: ኤሌክትሪክ፣ ሻማ፣ እንጨትና ሌሎች ብርሃንን በመስጠት ያገለግላሉ:: ሌሎችም ብዙ ሳይንስ ነክ ጥያቄዎች ስለሚኖሩ ከላይ በተመለከትናቸው መሠረት ሊጠኑ ይገባል:: ከሳይንስ ጋር የማይስማሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስህተት ናቸው ማለት አግባብ አይደለም::

## ኀ/ ተቃዋሚዎች ከመጽሐፉ ሲቀንሱ ወይም ሲጨምሩ እርስ በርሱ የሚጋጭ ይመስላቸዋል

መቼም መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም በጣም ቀላል ሥራ አይመስለኝም:: አንዱን ጥቅስ ወስደን ትርጉም መስጠት አስቸጋሪ ተግባር ነው::ምናልባት የራሳችን የሆነ ሐሳብ ይዘን መጥተን ሐሳቤን ደግፉልኝ ካላልነው በቀር እግዚአብሔር ሊናገረን የፈለገውን መልዕክት በደቂቃዎች ውስጥ መረዳት በጣም አዳጋች ይሆናል:: አንዳንድ ሙስሊም ጸሐፊዎች መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደሚተረጎም ሳያውቁ የሆነ ያልሆነውን ሲያስተምሩ

ይስተዋላሉ::በጣም የሚገርመው ግን አንዳንዶች በትክክል ጥቅስ መጥቀስ የማይችሉ ሆነው ሳሉ እስልምናን ለማስፋፋት ካላቸው ምኞት የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስን ስለ እስልምና እምነት እንዲ ደደግፍላቸው ያስገድዱታል:: እስቲ እናንተ ፍረዱ መጽሐፈ ቅዱስን በትክክል መጥቀስ ያልቻለ ሰው እንዴት ሥነ መለኮታዊ የሆነ ትርጉም መስጠት ይችላል? ከገጠመኞቼ አንዱን ላንሳ:: የመጽሐፉ ስም «ስሕተትን መመለስ ኦሪትና ወጌልን በመጥቀስ» የሚል ሲሆን ጸሐፊው አቶ ቀመር ሁሴን የተባሉ ሰው ናቸው:: እኚህ ሰው ዋናው ዓላማቸው ክርስትናን ሐሰት እስልምና እውነት እንደሆነ ማሳየት ነው:: ይህንን ዓላማ ለማሳካት መጽሐፍ ቅዱስን ከአውዱ ውጪ በመተርጎም የማይለውን እንዲል በማድረግ እስልምና ብቻ እውነተኛ እምነት መሆኑን ለማስረዳት ሞክረዋል:: ፀሐፊው በቂ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የላቸውም አሊያም አውቆ ለማሳሳት ጥቅሶችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲወስዱ ከቃሉ ጨምረው ወይንም ቀንሰው አሊያም በፍጹም የሌለ ነገር ጠቅሰው ጽፈዋል:: በመጽሐፋቸው ገጽ 25 ከ2ኛ ቆሮ.8:4 ጠቅሼዋለሁ ያሉት ጥቅስ እንዲህ ጽፈውታል:: ለጣኦታት «እንግዲህ የተሰዋውን ሥጋ ስለመብላት ጣኦታት ሁሉ በዓለም ላይ ከንቱ እንደሆኑና ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን:: መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ ነገር ግን በሰማይም ሆነ በምድር አማልክት የተባሉ ብዙ ቢኖሩ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን::» ነገር ግን በመ ጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮ.8:4 ያለው ቃል እንዲህ ይነበባል« ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይለምኑ ነበር::» አንባቢያን እናንተ ፍረዱ እነዚህ ጥቅሶች በምን ይመሳሰላሉ? ሌላ ልድገማችሁ - ከገጽ18-19 ከዮሐንስ ወንጌል 8:44 ወሰድኩት ያሉት ጥቅስ እንዲህ ይላል« ኢየሱስም መለሰ አለም እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው:: የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው:: አላወቃችሁትም እኔ ግን አውቀዋለሁ:: አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንኩ ነበር:: ዳሩ ግን አውቀዋለሁ ቃሉን እጠብቃለሁ::» በዮሐ.8:44 ያለው ጥቅስ ሌላ ነው:: እንዲህ ይነበባል:: «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያቢሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ::እርሱ ከመጀመሪያ

ነፍስ ገዳይ ነበረ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመ ም:: ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል:: ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና::» እነዚህን ክፍሎች በደንብ ተመልከቱዋቸው:: የመጀመሪያው ስለ ኢየሱስ ይናገራል የሁለተኛው ግን ስለ ሰይጣን እና አይሁድ ይተርካል:: በምን ይገናኛሉ? ውድ አንባቢያን እንግዲህ እኚህ ጸሐፊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ችግር ያለባቸው ነገር ግን ያለ የሌለውን በማምታታት እስልምናን ማስፋፋት አለብኝ ብሉ በግብታዊነት የተነሱ ይመስላሉ:: የአቶ ቀመር ሁሴን ስሕተት የሌለውን መጥቀሳቸው ብቻ ሳይሆን በቃሉ ላይ የሌለውን መጨመራቸውም ነው:: በገጽ 7 ከኢሳ.45:11 የጠቀሱት «የእግዚአብሔር ቃል ወደፊት ስለሚመጣው ነገር ጠይቁኝ..»ይላል በማለት ጽፈዋል:: ነገር ግን ከመጽሐፉ እንዲህ ይነበባል«የእሥራኤል ቅዱስ ሰሪውም እግዚ አብሔር እንዲህ ይላል:- የሚመጣውን ጠይቁኝ ...» .በዚህ ክፍል «የእግዚአብሔር ቃል" የሚለውን ሲጨምሩ "የእስራኤል ቅዱስ ሰሪውም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል::» የሚለውን ሐረግ ቀንሰዋል::ነገር ግን ለክርክራቸው እንዲመቻቸው የሌለውን ጨምረዋል::

በገጽ 14 ላይ ደግሞ ከዮሐ.14:15 ሲጠቅሱ ከቃሉ ቀንሰዋል:: ይህም ያደረጉበት ምክንያት ትምሕርታቸውን ስለሚያበላሽባቸው ነው:: የጠቀሱትም ቃል እንዲህ ይላል« እኔ አምላክን እለምናለሁ አጽናኝ ይሰጣችኋል» ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይነበባል «ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ::እኔም አብን እለምናለሁ ለዘለዓለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል::» አቶ ቀመር ሁሴን «አብን» የሚለው «አምላክ» በማለት ሲቀይሩ«ለዘለዓለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ» የሚለውን ሐረግ ቀንሰዋል:: በእርግጥም የሐሰት አስተማሪዎች ሥራ ከቃሉ መቀነስ መጨመር፣ ወይንም የሌለውን ማምጣት ስለሆነ በሥራቸው አልደነቅም:: ፈቃደኛ ቢሆኑ ወደ እውነት እንዲ መለሱ ለእርስዎም ደህንነት የሞተውን ከሞትም የተነሳውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያምኑ የዘወትር ጸሎቴና ምኞቴ ነው::

መቼም አቶ ቀመር ሁሴን የፈጸሙት ስሕተት ይህ ነው የማይባል ቢሆንም ሁለት ቦታ ላይ የቀየርዋቸውን ቃላቶች ተመልክተን ቀሪው ለእናንተ በመተው ጽሑፌን ለማጠቃለል እሞክረላሁ:: የመጀመሪያው ያለው ገጽ 23 ላይ ሲሆን የጠቀሱትም ከሐዋ.26:24 ሲሆን «ፊስጦስ» የሚለው ቃል «ጲላጦስ» ብለው ጽፈዋል:: ሁለተኛው ደግሞ ያለው ገጽ 26 ሲሆን የጠቀሱት ከዮሐ.12:47-49 ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል « የሚጥለኝ» ሲል ጸሐፊው የጻፉት «የሚጠላኝ» ብለው ነው:: እንግዲህ አቶ ቀመር ሁሴን ቃላቶችን የቀየሩት ሰዎችን ለማሳሳት ከሆነ ከዚህ ክፉ ተግባር እንዲመለሱ የእውቀት ችግር ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደሚተረጎም እንዲማሩ ለማሳሰብ እወዳለሁ:: በመጨረሻም አቶ ቀመር ሁሴንም ሆኑ ሌሎች ሙስሊሞች በሱራ2:136፣4:136፣10:94፣5:43-44 እና በሌሎች የቁርአን አንቀጾች እንደተጻፈላችሁ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኝነት ብትቀበሉ ለሕይወታችሁ ምክንያት ይሆንላችኋል::

ወገኖቼ እውነት በድምጽ ብልጫ እውነትነቱ አይረጋገጥም::ወይንም ብዙዎች ስለተቃወሙት እውነት ወደ ሐሰት አይለወጥም:: ደጋፊ ባይኖራትም እውነት በራስዋ ጸንታ ትኖራለች:: ድሮም ይሁን በዚህ ዘመን እውነት የሚመስሉ ነገር ግን ያልሆኑ አስተምህሮዎች በሰፊው ተሰራጭተው እናገኛለን:: እውነቱን የመፈለግና የመመርመር ሐላፊነቱ እግዚአብሔር ለእኛ ሰጥቶአል:: ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ፈቃድ ሰው ብቻውን አስቦበት ፣ ከሰዎች በመጠየቅ ወይንም ቅዱሳን መጽሐፍትን በማንበብ እንዲረዳ ይጠበቅበታል::

ብዙዎች እውነት ለሰዎች ሁሉ እንዳይገለጥ የስህተት አስተምህሮን በማስፋፋት ሰዎች ወደ እውነት እንዳይመጡ እያደረጉ ናቸው:: ከዚህም ሁሉ በላይ በዛቻና በማስፈራሪያ ከዚያ አስተምህሮ እንዳይወጡ የሰዎችን ሕይወት ያጎሳቁላሉ:: ለዘላለምም ለስህተት አስተምህሮ እስረኛ ያደርጋሉ:: ለሰዎች ነፃ

ፈቃድ የሰጠ አምላክ ከዚህ እምነት ውጪ ሌላ እምነት ውስጥ ቢሆን ይገደል ወይም ይሰደድ ይላልን?

ሙስሊሞችም በድፍረት እውነተኛው መንገድ የትኛው ነው ብላችሁ ልትጠይቁ የተሸሸገውን እውነት ገልጣችሁ በማየት ወደ እውነት ልትመጡ ይገባችኋልና:: አንባቢያን በስጋትና በማመንታት ውስጥ ያላችሁ እውነትን ለመረዳት ጥያቄዎችን ጠይቁ፣ መርምሩ፣ አትፍሩ፣ ነፃ የሚያወጣውን እውነት ለማወቅና ለመቀበል ቁርጠኛነት ይኑራችሁ:: መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስተምር ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ አንድ መንገድ ብቻ እንደሆነ እርሱም ክርስቶስ እንደሆነ በዮሐ.14:6 እንዲህ ይላል:- " ኢየሱስም እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ" ክርስቶስ ስለ ሁላችን ኃጢአት በመስቀል ላይ በመሞት ከእግዚ አብሔር ጋር አስታረቀን:: እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የደህንነት ተስፋ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈጸመው:: / ዘፍ.12:1-4/ ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: ስለዚህም እግዚአብሔር አንድያ ልጁ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት መስዋዕት እንዲሆን እንደሰጠ በዮሐ.3:16 እንዲህ ይለናል:-" በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና"

ይህንን የደህንነት መንገድ ያልተቀበሉ ሰዎች የሚገጥማቸው አደጋ መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐ.3:36 እንዲህ ይገልጸዋል:- " በልጁ የማያምን የዘላለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚ አብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም:: "የደህንነት ብቸኛው መንገድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው:: ያላመኑት በእግዚአብሔር ቁጣ ውስጥ ይኖራሉ:: ያመኑት ግን በሰላምና በደስታ ውስጥ ይኖራሉ::

ወገኖቼ ወደ ዘላለም እረፍት ኑ እረፉም ጌታ ያሳርፋችኋልና:: አስተያየት ወይንም ጥያቄ ያላችሁ ለአንዋር መሐመድ ፖ.ሣ.ቁ.698 አዲስ አበባ ብላችሁ ጻፉልን::

# ዋቢ መጻሕፍ


Ali, Abdella Yusuf. The Holy Quran-An English translation of the meaning and commentary. Al-Munawarah:king fahd Holy Quran printing complex,1410A.H.

Campbell,DB.William. The Quran and the Bible in the light of histroy and science.

Dewitt,David A. Answering the tough ones. Chicago: The moody Bible institute, 1980.

Esack,Farid. The Quran a short introduction. Oxford:oneworld publications, 2002.

Gaebelein, Frank E.The expositor's Bible Commentary. Vol.3-6,8,9. Grand Rapids:Zondervan pub. house,1986

Gaebelein, Frank E. The expositor's Bible Commentary. Vol.2, Grand Rapids: Zondervan publishig House, 1990.

Geisler,Norman. Christian a pologetics. Grand Rapids: Baker Book house, 1976.

Geisler, Norman and Thomas Home. When critics ask. USA: victory Books,1992

Gil christ,John. Facing the Muslim Challenges. Capetown: life challenge Africa,2002.

Gil christ,John. The texual history of the Quran and the Bible.Villach: Light of life,1988.

G.J Wenhan, J.A.Motyer and others. New Bible Commentary. Leicester: Inter-Varsity press,1994.

Holy Quran ( Amharic).Addis Ababa: Artistic printing Ltd,1968 ( 1961 E.C)

Holy Bible ( Amharic) Addis Ababa: Birhan and Selam printing press, 1962.

John Peter Lange, D.D. Langer`sCommentary on the Holy Scriptures Vol.3-9 Grad Rapids: Zondervan. pub. House, 1971.

Kaiser Jr. Walter. Peter H.Davids and others. Hard sayings of the Bible. Downers grove: Inter- Varsity press, 1996.

Dr.Khan, Muhamad Muslim. The translation of the meaning of sahih al-Bukhari Arabic English. Vol.1-9

Mcdowell, Josh. Reasons why Skeptics out to consider Christianity. San Bernardino: Here`s life publishers, 1981.

Mcdowell, Josh. Christianity a ready defenece. Uk: Scripture Press foundation, 1990.

Mcdowell, Josh and John Gillchrist. The Islam Debate. San Bernardino: Here`s life publishers, 1983.

13. Light of Life, False charges against the new Testament, 1992, pp.82-83; Frank E.Gaebecin, the expositor's Bible commen tary, 1984,p.296;Josh MlcDowell and John Gilchrist,The Islam deabate, 1983, p.125.
14. Josh McDowell and John Gilchrist, The Islam Debate, 1983, p.165
15. J.C.Ryle. Expository thoughts on John, Vol.3,1987, pp.320-31.
16. Josh MCDowell and john Gilchrist, The Islam Debate, 1983, p.85
17. John N.Qswalt. The New international Commentary ( Isaiah), 1986, pp.394-395.
18. John N.Qswalt. The New international Commentary ( Isaiah), 1986, p.217
19. Frank E.Geabelein, The expositor's Bible Commentary, Vol.2, 1990, pp.483-484
20. J.C. Ryle,Expository Thoughts on John Vol.1, 1987, p.7